# Basic Elements of Imamu Shafi Fiqh

# የኢማሙ ሻፍኢ ፊቅህ መሰረታዊ ክፍሎች




Presented by: Youth-Mission Online Amharic Islamic Books Publishing.

# Basic Elements of Imamu Shafi Fiqh

# የኢማሙ ሻፍኢ ፊቅህ መሰረታዊ ክፍሎች


አዘጋጅ: ኡመር አብዱል ጀባር

ትርጉም በአህመድ የሱፍ



All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ



የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008

ሰሜን ወሎ ወልዲያ



ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323



http://youth-mission.mobie.in


ይህ መጽሐፍ ስለ ኢስላም ግንዛቤ ለሌላቸው ሰዎች እጥር ምጥን ባለ መልኩ እውቀት የሚያገኙበት እውቀት ያላቸውም ለመሸምደድ የሚያመች በመሆኑ እውቀታቸውን የበለጠ የሚያዳብሩበት ወይም ለማስተማር የሚረዳ ሆኖ ስላገኘሁት ወደ አማርኛ ተርጉሜዋለሁ። ጠቃሚ ሆኖ እንደምታገኙት ተስፋ አደርጋለሁ።

በዚህ መፅሐፍ ከተዳሰሱ አርዕስቶች መካከል የኢስላም ምንነት ፍች ፣ አምስቱ የኢስላም ህጎች ፣ ጦሃራ ፣ የቆሻሻ አይነቶችና የማስወገጃ መንገዶቻቸው ፣ ኢስቲንጃ ፣ ውዱዕ ፣ ጉሱል ፣ ተየሙም ፣ ሶላት ፣ አርካኑ ሶላት ፣ የኢድ ሶላቶች ፣ ዘካና ሃጅ ወ.ዘ.ተ አርዕስቶች ተዳሰውበታል። በየምዕራፉ የተነሳውን አርዕስት ምንያህል እንደተረዳነው እራሳችነን ለመፈተሽ ከእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ጥያቄዎች ተካተውበታል። አንብበን የምንጠቀምበትና ሌሎች እህት ወንድሞቻችነን የምንጠቅምበት ያድርግልን።

# የኢማሙ የሻፊ ፊቅህ መሠረታዊ ክፍሎች


**አዘጋጅ: ኡመር አብዱል ጀባር**

**ትርጉም በአህመድ የሱፍ**


## ክፍል አንድ

## የኢስላም መሠረታዊ ነገሮች

**ኢስላም**: ማለት ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ላመጡት አስተምህሮት እራስን ማስገዛት ሲሆን ያዘዙትን መታዘዝ፤ የከለከሉትን መከልከል ነው።

**የኢስላም አራት መሰረታዊ ክፍሎች አሉት። እነሱም፡-**

1. አል-ቁርአን
2. ሐዲስ
3. ኢጅማ
4. ቂያስ

**ቁርአን**: ለመጨረሻው መልዕክተኛ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የተገለፀ ቅዱስ የአሏህ መጽሐፍ ሲሆን መጽሐፉ በሃይማኖትና በአለማዊ ጉዳዮች ላይ ለሰዎች መመሪያ የሆነ ነው።

**ሐዲስ**: የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ንግግርና ተግባር ሲሆን የቁርአን አስተምህሮትን ያብራራል፤ የሰው ልጆችን ወደ ትዕዛዞቹ ያመላክታል።

**ኢጅማ**: በሃይማኖቱ ጉዳይ ኡለማዎች የተስማሙበት ሲሆን አብዛሃኛው ሙስሊም አንድ የሚሆኑበት ማለት ነው።

**ቂያስ**: ማለት ለሁክም (ለፍርድ) ይሆን ዘንድ በኢስላም ግልፅ ማስረጃ የሌላቸውን ጉዳዮች ከተመሳሳይ ጉዳዮች ጋር ማመዛዘን ነው።

## ጥያቄና መልስ

1) ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?
2) የኢስላም መሰረታዊ ክፍሎች ምንድን ናቸው?
3) ቁርአን ምንድነው?
4) የሐዲስ ፣ የኢጅማንና የቂያስ ፍች ምንድነው?

## ክፍል ሁለት

አምስት አይነት የኢስላም ህጎች አሉ። እነሱም

1. ፈርድ
2. ሱና
3. ሐራም
4. መክሩህ
5. ሙባህ

**ፈርድ** ማለት ቢሰሩት የሚመነዱበት ቢተውት የሚቀጡበት ህግ ሲሆን በኢማሙ ሻፊኢ ፊቅህ መሰረት ፈርድና ዋጅብ የሚያመላክቱት ተመሳሳይ ነገር ነው የሐጅ ምዕራፍ ላይ ሲቀር።

**ሱና** ማለት ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እና እነዛ ብርቅየ ሶሃባዎች(ረ.ዐ) የኖሩበት መንገድ ማለት ነው። ሱና መንዱብና ሱና ሙስተሃብ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው።

**ሐራም** መጥፎ ስራ ከመስራት የሚቆጠብ ሰው የሚመነዳበት ሲሆን ለሚፈፀመው ደግሞ የሚቀጣበት ነው።

**ሙባህ** ቢሰሩትም ባይሰሩትም ምንዳም ቅጣትም የሌለው ማለት ነው።

**መክሩህ** ቢሰሩት የማይቀጡበት ነገርግን ቢጠነቀቁት ወይም ቢተውት የሚመነድበት ነው።

## የፈርድ አይነቶች

ሁለት የፈርድ አይነቶች አሉ።

1. ፈርደል አይን
2. ፈርደል ኪፋያ

## ጥያቄና መልስ

1) ስንት የኢስላም ህጎች አሉ? እነማን ናቸው?
2) የፈርድ ፣ የሱና ፣ የሐራም ፣ የመክሩህና የሙባህን ፍች ግለፁ?
3) ስንት የፈርድ አይነቶች አሉ?
4) ፈርዶል አይን ምንድነው?
5) ፈርዶል ኪፋያ ምንድነው?

## ክፍል 3

## ጦሃራ

ሶላታችን ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ እራሳችነን ከቆሻሻ የምናነፃበት ልዩ ዘዴ ሲሆን ሁለት አይነት የንፅህና አይነቶች አሉ። እነሱም ከማይታይ ቆሻሻ መንፃት(መታጠብ)ና ከሚታይ ቆሻሻ መንፃት ወይም መታጠብ ናቸው።

**ከሃደስ** መንፃት ውዱእ በማድረግ ገላን በመታጠብ ወይም ደግሞ ተየሙም በማድረግ እራስን ከቆሻሻ ማንፃት ነው።

**ከሐደስ መታጠብ(መንፃት)** ማለት ከሆድ ውስጥ ያለውን ቆሻሻ (ሽንትና አይነምድር) ካስወገዱ ብኋላ ወይም ልብስና መስገጃ ቦታ ላይ ያለውን ቆሻሻ ካስወገዱ ብኋላ እራሳን ማንፃት ወይም መታጠብ ነው።

## የሙጧሃራት(የቆሻሻ ማስወገጃ) አይነቶች

1. ንፁህ ውሃ
2. ንፁህ አፈር
3. ንፁህ ድንጋይ
4. ቆዳ

## የውሃ አይነቶች

ሶስት አይነት የውሃ አይነቶች አሉ።

1. ውሃው እራሱ ንፁህ የሆነና ለመታጠቢያነት የሚያገለግል
2. ውሃው ንፁህ ሆኖ ነገርግን ለመታጠቢያነት የማያገለግል
3. የተበከለ ውሃ

## ውሃው በራሱ ንፁህ የሆነና ለመታጠቢያነት የሚያገለግል

ከሆነ ነገር ጋር ባለመቀለቀሉ ምክኒያት ባህሪውን ያልቀየረ ማንኛውም የዝናብና የምንጭ ውሃ። ልክ እንደዚሁ የባህር ውሃ ፣ የወንዝ ውሃ ፣ የበረዶ ውሃ ወ.ዘ.ተ

## የተቀየረ ነገርግን ለመታጠቢያነት የሚያገለግል ውሃ

ውሃን ከሚበክሉ ማናቸውም ነገሮች ጋር በመቀላቀሉ ምክኒያት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ባህሪውን የተቀየረ ውሃ ሆኖ ነገርግን ለመታጠቢያነት የሚያገለግል እንደሚከተለው ነው።

1. ለረዥም ጊዜ የማይንቀሳቀስ በመሆኑ ወይም የአሳዎችና የእንቁራሪቶች መራቢያ በመሆኑ የተቀየረ ውሃ
2. ውሃው በሚያርፍበት ወይም በሚፈስበት መፋሰሻ ምክኒያት የተቀየረ ውሃ ወይም ደግሞ ከሸክላ አፈርና ከጨው ጋር የተቀላቀለ ውሃ
3. በንፋስ አማካኝነት ልናስወግድ ከማንችላቸው ነገር ጋር በመቀላቀሉ የተቀየር ውሃ። ለምሳሌ ውሃው ላይ የሚያርፍ የዛፍ ቅጠል

4. የወደብ መልክ የያዘ ውሃ ወይም የተቀባ ገንዳ መልክ የያዘ ውሃ
5. ባቅራቢያው ወድቆ በሚገኝ ቆሻሻ ምክኒያት የተቀየረ ውሃ። በንፋስ ምክኒያት ጠአም ካለው ነገር ጋር የተቀላቀለ ውሃ ወ.ዘ.ተ

**ውሃው ንፁህ ሆኖ ነገርግን ለመታጠቢያነት የማያገለግል**

ውሃው ንፁህ ሆኖ ነግርግን ለመታጠቢያነት የማያገለግሉ ሶስት የውሃ አይነቶች አሉ። እነሱም፡-

1. ከስኳር ፤ ከማር ፤ ወ.ዘ.ተ ጋር በመቀላቀሉ ምክኒያት ሙሉ በሙሉ የተቀየረ ውሃ
2. ቀደም ብለን ለመታጠቢያነት የተገለገልንበት አነስተኛ መጠን ያለው ውሃ
3. የተለያየ ዘዴን በመጠቀም ከዛፍ የሚወጣ ውሃ ለምሳሌ የሮዝና የኮክነት ውሃ

**የተበከለ ውሃ**

የተበከለ ውሃ ሁለት አይነት ነው።

1. የቆሻሻው መጠን ትንሽም ይሁን ትልቅ ውሃው ውስጥ በመውደቁ ወይም ውሃው ጋር በመዳለቁ ምክኒያት ባህሪው የተቀየረ ውሃ
2. ምንም እንኳ ውሃው ባህሪውን ባይቀይርም የውሃው መጠን ትንሽ ሆኖ ቆሻሻ ያረፈበት ውሃ

## ጥያቄና መልስ

1) ጦሃራ ምንድነው?
2) የሐደስ ትጥበት ማለት ምን ማለት ነው?
3) ከሑቡስ መንፃት ማለት ምን ማለት ነው?
4) ለመታጠቢያነት ወይም ለመፅዳጃነት የሚያገለግሉ ምንምን ናቸው?
5) ውሃው ንፁህ ሆኖ ነገርግን ለመታጠቢያነት የማያገለግል ምን አይነት ውሃ ነው?
6) የተበከለ ውሃ ምን አይነት ነው?
7) ውሃው ባህሪውን ቀይሮ ነገርግን ንፅህ የሆነ ውሃ ምን አይነት ነው?

# ክፍል 4

## ነጃሳ

ሶስት የነጃሳ (የቆሻሻ) አይነቶች አሉ።

1. ሙጋለዟ
2. ሙሃፈፋ
3. ሙተዋሲጧ

**ሙጋለዟ:** የውሻና የአሳማ ልጋግና ላብ ነው። እነዚህ ሁለት እንስሳቶች ከሌሎች ንፁህ እንስሳቶች ጋር ተዳቅለው ቢወለዱም እንኳ ያው ሙጋለዟ ናቸው።

**ሙጋለዟን የምናነፃበት መንገድ**

በዚህ ቆሻሻ የተበከለ እቃ ሰባት ጊዜ መታጠብ አለበት። ስድስት ጊዜ በንፁህ ውሃ ቆሻሻውን ካስወገዱ ብኋላ አንድ ጊዜ በንፁህ አፈር መታጠብ ይኖርበታል።

**ሙሃፈፋ:** ሁሉት አመት እድሜ ያልሆነው የሚጠባ ልጅ ሽንት አይነት ነው።

**ሙሃፈፋን የምናነፃበት መንገድ**

በዚህ አይነት ቆሻሻ የተበከለ ቦታ እስኪረጥብ ድረስ ውሃ ሊያርከፈክፉበት ይገባል።

**ሙተዋሲጧ**

ሁለት የሙተዋሲጧ አይነቶች አሉ።

1. ሁክሚያ
2. አኒያ

**ሁክሚያ:** ቅርፅ ፣ ጣዕምና ሽታ የማይኖረው ቆሻሻ ነው። ለምሳሌ ጡት ከሚጠባ ልጅ ውጭ የሆነ ሽንት ሆኖ ሲደርቅ ቅርፅ የማይኖረው ነው።

### ሁክሚያን የምናነፃበት መንገድ

በዚህ ቆሻሻ የተበከለ ቦታ ወይም እቃ አንዴ በውሃ ቢታጠብ ንፁህ ይሆናል።

**አኒያ:** ቅርፅ ፣ መልክ ፣ ጣዕምና ሽታ ያለው ቆሻሻ ነው። ለምሳሌ አይነ ምድር ፣ ፍግ ፣ ደም ፣ መግል ፣ ትውኪያ ፣ አስካሪ መጠጥ ፣ መዝይ ፣ ወድይ ፣ ማንኛውም የሞተ ጥንብ ከሰው ፣ ከአሳና ከአንበጣ በቀር ያልተፈቀደ እንስሳ ወተት ወ.ዘ.ተ

### አንያን የምናነፃበት መንገድ

በዚህ ቆሻሻ የተበከለ ቦታ ወይም እቃ ሙሉ በሙሉ እስኪለቅ ድረስ በውሃ መታጠብ ይኖርበታል። የቆሻሻው ምልክት ቦታው ላይ ወይም ልብሱ ላይ ቢቀርም ችግር የለውም።

### የወይን መጠጥን የምናነፃበት መንገድ

ወይን ወደ ሆምጣጣነት ሲቀየር ንፁህ እንደሆነ ይቆጠራል።

### ቆዳን የምናነፃበት መንገድ

ከወአሳማ ፣ ከውሻና ከዝርያዎቻቸው ቆዳ በቀር የእንስሳት ቆዳ ከለፋ በኋላ ንፁህ እንደሆነ ይቆጠራል።

## ጥያቄና መልስ

1) ስንት የነጃሳ (የቆሻሻ) አይነቶች አሉ?
2) የሙጋለለዟ ቆሻሻ ምንድነው?
3) ሙጋለለዟ የሚፀዳበትን መንገድ ግለፅ?
4) የሙሃፈፋ ቆሻሻ ምንድነው? እንዴት ነው የምናፀዳው?
5) ስንት አይነት የሙተዋሲጧ የቆሻሻ አይነቶች አሉ?
6) የሁክሚያ ቆሻሻ ምንድ ነው? እንዴት ነው የሚፀዳው?
7) የአኒያ ቆሻሻ ምን እንደሆነና የሚነፃበትን መንገድ ግለፁ?
8) የእንስሳት ቆዳ የሚነፃበትን መንገድ አብራራ?

# ክፍል 5

## ኢስቲንጃ

ኢስቲንጃ: ማለት ሽንት ቤት ከተጠቀሙ ብኋላ ሃፍረተ ስጋን በውሃ ፣ በድንጋይ ወይም በሌሎች ነገሮች የማፅዳት ተግባር ነው።

## የኢስቲንጃ አደራረግ ሁኔታ

ቆሻሻውን ለማስወገድ በሶስት ንፁህ ድንጋዮች ሃፍረተ ገላን ማበስ። ከዚያ ብኋላ ሃፍረተ ገላን በንፁህ ውሃ ማጠብ። ኢስቲንጃ ለማድረግ ከሁለቱ አንዱን መጠቀም የሚቻል ቢሆንም ውሃን መጠቀሙ ግን በላጭ ነው።

## በድንጋይ ኢስቲንጃ ለማድረግ ቅድመ ሁኔታዎቹ

1. ቆሻሻው መድረቅ ወይም መዛመት የለበትም
2. ድንጋዩ ከቆሻሻ ንፁህ መሆን አለበት
3. ቆሻሻው ከሃፍረተ ገላ (ከብልት) ውጭ መነካካት የለበትም
4. ድንጋዩ ደረቅና ንፁህ መሆን አለበት።

ህይወት የሌለውና እንደ ቅዱስ የማይቆጠር ማንኛውም ንፁህ የሆነን ነገር ከድንጋይ በተጨማሪ እንደ አማራጭ መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ወረቀት ፣ እንጨት ወ.ዘ.ተ

## ኢስቲንጃ በማድረግ ውስጥ ያሉ የሱና ተግባራቶች

1. መፅዳጃ ቤት በግራ እግር መግባትና በቀኝ እግር መውጣት
2. መፅዳጃ ቤት ከመግባት በፊት ቢስሚላህ አሏሁመ ኢኒ አኡዙ ቢከ ሚነል ኹቡሲ ወል ኸባኢሲ የሚለውን ዱአ ማንበብ
3. መፅዳጃ ቤት በለለበት ወቅት ሰው በማያይበት ፣ የፅዳጁ(የአይነምድሩ) ድምፅና ሽታ በማይሰማበትና በማይሸትበት ድብቅ በሆነ ቦታ መፅዳዳት
4. ኢስቲንጃ ለማድረግ ቀኝ እጅን መጠቀም
5. ከሽንትም ሆነ ከአይነ ምድር ጠብታ እራስን መጠበቅ

**እስቲንጃ በማድረግ ውስጥ የተጠሉ ተግባራቶች**

1. ብዙ መጠን ያለው ውሃ ላይ መሽናት
2. ሽንት ቤት ውስጥ የአሏህን ስም የያዘ ነገር ይዞ መግባት
3. ወደ ቂብላ መዞር ወይም ጀርባን ወደ እሱ ማዞር
4. ወደ ንፋስ አቅጣጫ መዞር
5. መናገር
6. ምንም ሳያስፈልግ አሁንም አሁንም መትፋት
7. ወደ ሰማይ መመልከት
8. ፍሬ ያዘለ ዛፍ ጥላ ስር ወይም ሰዎች የሚቀመጡበት ጥላ ያለው ዛፍ ስር መፅዳዳት

## ጥያቄና መልስ

1) ኢስቲንጃ ምንድ ነው?
2) ኢስቲንጃ የሚደረገው እንዴት ነው?
3) በድንጋይ ኢስቲንጃ ለማድረግ ቅድመ ሁኔታው ምንድነው?
4) በኢስቲንጃ ውስጥ ያሉ የሱና ተግባራቶች ምንምን ናቸው?
5) በኢስቲንጃ ውስጥ መክሩህ የሆኑ (የተጠሉ) ነገሮችን ግለፁ?

# ክፍል 6

# ውዱእ

### የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች

ውዱእ ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው ይሆን ዘንድ አምስት ቅድመ ሁኔታዎች አሉት። እነሱም፡-

1. ሙስሊም መሆን
2. ጠንካራ መሆን
3. ውዱእ በማድረግ የሚታጠቡ የአካል ክፍሎች ውሃው ሙሉ የአካል ክፍሎች ላይ እንዳይደርሱ የሚያደርጉ ነገሮችን ማስወገድ
4. ፈርድ የሆነውን የውዱ ክፍል እንደ ሱና አለመመልከት

### በውዱእ  ውስጥ ግዴታ የሆኑ ተግባራቶች

በውዱ ውስጥ ልንፈፅማቸው የሚገቡ ስድስት ተግባራቶች አሉ። እነሱም፡-

1. ከመታጠብ በፊት የውዱ ኒያ ማድረግ
2. ከግንባር ፀጉር መብቀያ አንስቶ እስከታችኛው አገጭ ድረስና ከአንደኛው የጆሮ ጉትቻ ጀምሮ እስከ ሌላኛው ያለውን ሙሉ ፊትን ማጠብ
3. እጆችን እስከ ክርን ድረስና በረዥም ጥፍር የተሸፈኑ የጣት ጫፎችን ማጠብ
4. ፀጉር ኖረውም አልኖረውም እራስን ማበስ
5. ቁርጭምጭሚትንና ተረከዝን ጨምሮ ሁለቱንም እግሮች ማጠብ
6. ከላይ የተጠቀሱትን አራቱን ክፍሎች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ ማከናዎን

### በውዱ ውስጥ ሱና የሆኑ ተግባራቶች

1. ቢስሚላህ (በአሏህ ስም) ብሎ መጀመር
2. ሁለቱንም እጆች እስከ እጅ አንጓ ድርስ መታጠብ

3. ሲዋክ መጠቀም

4. መጉመጥመጥ

5. ውሃ በአፍንጫ ማስገባት ማስወጣት

6. ሙሉ እራስን ማበስ

7. የጆሮን የውስጠኛውንም ሆነ የላይኛውን ክፍል ማበስ

8. የእጅና የእግር ጣቶችን ኸላል ማድረግ

9. ጥቅጥቅ ያለ ፂምን ኸላል ማድረግ

10. ቀለበትን ማሽከርከር

11. ቀኝ እጅን በመጀመሪያ መታጠብ

12. እያንዳንዱን ተግባር ሶስት ጊዜ መድገም

13. ቀድሞ የታጠበው የአካል ክፍል ከመድረቁ በፊት ቀጣዩን የአካል ክፍል ማጠብ

14. ሲታጠቡ የአካል ክፍልን ማሸት

15. ውዱእ ከጨረሱ ብኋላ ዱአ ማድረግ

## በውዱ ውስጥ የተጠሉ ተግባራቶች

1. ውሃ ከሚያስፈልገው በላይ መጠቀም(ማባከን)
2. ያለምንም ተጨባጭ ምክኒያት ውዱእ ለማድረግ የሰውን እርዳታ መሻት
3. አንድን የአካል ክፍል ከሶስት ጊዜ በላይ ማጠብ
4. አካልን ማድረቅ

## ውዱእ የሚያበላሹ ነገሮች

ውዱ የሚያፈርሱ ነገሮች አራት ናቸው፡፡

1. ከሃፍረተ ስጋ (ከብልት) ውስጥ የሚወጣ ማንኛውም ነገር

2. አስካሪ መጠጥ በመጠጣት መታመም ፣ መተኛትና እራስን መሳት
3. የተቃራኒን ፆታ እጅ ያለምንም ከለላ መጨበጥ
4. ሃፍረተገላን( ብልትን) በመዳፍ ወይም በእጅ ጫፎች መንካት

## ጥያቄና መልስ

1) ውዱ ለማድረግ ምንያህል ቅድመ ሁኔታዎች አሉት?
2) በውዱ ውስጥ ምን ያህል ፈርድ የሆኑ ነገሮች አሉ?
3) በውዱ ውስጥ ምንያህል የሱና ተግባራቶች አሉ?
4) በውዱ ውስጥ ምን ያህል የተጠሉ ተግባሮች አሉ?
5) ውዱእ ሊያፈርሱ የሚችሉ ነገሮች ምንምን ናቸው?

# ክፍል 7

# ጉስል(የገላ ትጥበት)

### ጉሱል (ሙሉ ትጥበት) ግዴታ የሚያደርጉ ነገሮች

1. የወንድ ብልት ከሴቷ ብልት ውስጥ መግባት
2. የዘር ፈሳሽ(sperm) መርጨት
3. አንድ ሙስሊም ሰማዕት ሆኖ ሳይሞት ሲቀር
4. ሃይድ(የወር አበባ) መምጣት
5. ከወሊድ ቡኋላ ደም መፍሰስ
6. ልጅ መውለድ

**በጉሱል አደራረግ ውስጥ ግዴታ የሆኑ ነገሮች**

በጉሱል አደራረግ ውስጥ ግዴታ የሆኑ ነገሮች ሁሉት ናቸው። እነሱም፡-

1. የመጀመሪያውን የአካል ክፍል ሲታጠብ ኒያ ማድረግ
2. ውሃው ሙሉ የአካል ክፍልና የፀጉር ስር ድረስ እንዲ ደርስ ማድረግ

**በጉሱል አደራረግ ውስጥ ሱና የሆኑ ነገሮች**

በጉሱል አደራረግ ውስጥ ብዙ የሱና ተግባራቶች አሉ። ከእነሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1. ኢስቲንጃ ማድረግ
2. ሻወር ከመውሰድ በፊት ውዱእ ማድረግ
3. አካልን ማሸት
4. በቀኝ ጎን መጀመር
5. የራስ ፀጉር ላይ ሶስት ጊዜ ውሃ ማፍሰስ
6. ቀጣዩን የአካል ክፍል መታጠብ

የውዱእ ቅድመ ሁኔታዎች ለጉሱልም(ለገላ ትጥበት) ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። እንዲሁም በውዱእ ውስጥ መከሩህ(የተጠሉ) ነገሮች በጉስልም ውስጥ መከሩህ ናቸው።

## ጥያቄና መልስ

1. የገላ ትጥበትን ግዴታ የሚያደርጉ ነገሮች ዘርዝር?
2. በጉሱል (በገላ ትጥበት) ውስጥ ግዴታ የሆኑ ነገሮች ምንያህል ናቸው?
3. በጉሱል ውስጥ ሱና የሆኑ ምን አይነት ተግባራቶች ናቸው?
4. ጉሱል ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሊያሟላቸው የሚገቡ ነገሮችን ግለፅ?
5. በጉሱል ውስጥ የሚጠሉ ተግባራቶች ምንምን ናቸው?

# ክፍል 8

## ተየሙም

**ተየሙም** ልዩ በሆነ መንገድ በንፁህ አፈር እጅንና ፊትን ማበስ ሲሆን የውዱና የጉሱል አማራጭ ነው።

**ተየሙም እንዲፈቀድ የሚያደርጉ ነገሮች**

1. የውሃ መጥፋት
2. በህመም ምክኒያት ውሃውን መጠቀሙ በሽታውን ያገረሽብኛል ብሎ መፍራት
3. ቤት ውስጥ ላሉ እንስሳቶች ብቻ የሚሆኑ ጥቂት ውሃ መኖር

**የተየሙም ቅድመ ሁኔታዎች**

1. ተየሙም ከማድረግ በፊት ውሃ መፈለግ
2. በንፁህና በላመ አፈር ተየሙም ለማድረግ መነየት
3. የሶላት ወቅት ከጀመረ ብኋላ ተየሙም ማድረግ
4. ለእያንዳንዱ የፈርድ ሶላት ተየሙም ማድረግ

**በተየሙም ውስጥ ግዴታ የሆኑ ነገሮች**

1. ኒያ ማድረግ
2. መሬት ላይ ሁለቱንም መዳፎች ሁለት ጊዜ መምታትና ፊትንና ሁለቱንም እጆች እስከ ክርን ድረስ ማበስ
3. ተየሙም ሲያደርጉ የአካል ክፍል ላይ ያበሱትን አቧራ ማሸት
4. ተየሙም ሲያደርጉ ቅደም ተከተሉን መጠበቅ

**ተየሙምን የሚያፈርሱ ነግሮች**

1. ውዱእ የሚያፈርሱ ነገሮች ተየሙምንም ያፈርሳሉ
2. ሶላት ከመጀመር በፊት ውሃ ማየት (ማግኘት)
3. ክህደት(መክፈር)

**ውዱና ተየሙምን አንድ ላይ ማጣመር**

የቆሰለውን የአካል ክፍል በተየሙም አብሶ ቀሪውን የአካል ክፍል በውሃ ማጠብ

**በፕላስተርና በፋሻ የታሸገ የአካል ክፍል**

አካሉ በፕላስተርና በፋሻ የተሸፈነ ሰው ተየሙም አድርጎ በፕላስተሩ ወይም በፋሻው ላይ ማበስ ይኖርበታል። ፕላስተሩ ወይም ፋሻው ተየሙም የማይደረግበት ቦታ ላይ ከሆነና ጦሃራ ከሆነ ካበስነው ተየሙም ካደረግን ብኋላ ደግመን ማበሱ አያስፈልግም።

## ጥያቄና መልስ

1) ተየሙም ምንድን ነው?
2) ተየሙም እንዲፈቀድ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
3) የተየሙምን ቅድመ ሁኔታ ዘርዝር?
4) ተየሙም ውስጥ ግዴታ የሆኑ ነገሮች ምንምን ናቸው?
5) ተየሙምን የሚያፈርሱ ነገሮች ምንምን ናቸው?
6) ውዱእና ተየሙምን አጣምሮ የሚያደርገው ምን አይነት ሰው ነው?
7) ፕላስተር ወይም ፋሻ በለበሰ ሰው ላይ ያለው ህግጋት ምንድነው?

# ክፍል 9

## ሐይድና ኒፋሷ

**ከሴት ልጅ ማህፀን የሚፈሱ ሶስት አይነት ደሞች ናቸው።**

1. ሐይድ
2. ኒፍሷ
3. ኢስቲሃዷ

**ሐይድ:** ማለት አንዷት ወጣት እድሜዋ 9 ወይም 15 የሆነች ሴት በተፈጥሮ ከማህፀኗ የሚፈሳት ደም ነው።

**ኒፋሷ:** ከወሊድ ብኋላ ከሴት ልጅ ማህፀን የሚፈስ ደም ሲሆን የወሊድ ደም እየተባለ ይጠራል።

**ኢስቲሃዷ:** በህመም ወይም በበሽታ ምክኒያት ሴት ልጅ የሚፈሳት ደም ነው።

የሐይድ ጊዜ ቢያንስ ለአንድ ቀንና ሌሊት የሚቆይ ሲሆን በጣም ቆየ ሲባል ደግሞ 15 ቀንና ሌሊት ሊሆን ይችላል። አስራ አምስት ቀንና ከዛ በላይ ከሆነ ግን የኢስቲሃዷ (የበሽታ ደም) ነው የሚሆነው። እንዲሁም የእርግዝና ጊዜ አነሰ ቢባል ስድስት ወር ሲሆን በጣም ቆየ ከተባለ ደግሞ አስር ወራት ነው።

**በትንሹ ሃደስ ላይ ሁኖ ማከናዎን የተከለከሉ ተግባራቶች**

1. ሶላት መስገድ
2. ጠዋፍ ማድረግ
3. ቁርአን መንካትም ሆነ መያዝ

**ጁኑብ ለሆነ ሰው የተከለከሉ ተግባራቶች**

የሚከተሉት የአምልኮት ተግባራት በትልቁ ሐደስ ላይ ላለ ሰው የተከለከሉ ነገሮች ናቸው፡፡

1. ሶላት መስገድ
2. ጠዋፍ ማድረግ
3. ቁርአን መያዝም ሆነ መንካት
4. ቁርአን መቅራት
5. መስጅድ መግባት

**በሐይድና በኒፋሷ ወቅት የተከለከሉ ነገሮች**

1. ሶላት መስገድ
2. ጠዋፍ ማድረግ
3. ቁርአን መያዝም ሆነ መንካት
4. ቁርአን መቅራት
5. መስጅድ መግባት
6. መፆም
7. በሚስት ከእንብርቷ እስከ ጉልበቷ ባለው የአካል ክፍል መካከል አለመደሰት

## ጥያቄና መልስ

1) ስንት አይነት የሴት ልጅ ደም አለ?
2) ሐይድ ምንድነው?
3) ኒፋሷና ኢስቲሃዷ ምንድ ነው?
4) የእርግዝና ጊዜ ምንያህል ነው?
5) በሃደስ አስገር ወቅት የተከለከሉ የአምልኮት ተግባራት ምንምን ናቸው?
6) በጀናባ ፣ በሐይድና በኒፋሷ ወቅት የተከለከሉ ተግባራትን ጥቀሱ?

## ክፍል 10

## ሶላት

### አምስት አውቃ ሶላት

በቀን አምስቱ ሶላቶች በእያንዳንዱ ጤናማ አዕምሮ ባለውና ለአካለ መጠን በደረሰ ሙስሊም ላይ ሁሉ ግዴታ ናቸው፡፡ ግዴታ የሆነውን ሶላት የማይቀበል ወይም የሚክድና የማይሰግድ ሰው እንደ ካፊር (እንደ ከሃዲ) ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ልጆች እድሜያቸው ሰባት ዓመት በደረሰ ጊዜ ሶላት እንዲሰግዱ ይታዘዛሉ፡፡ እድሜያቸው አስር ሲሆን ሶላትን ችላ የሚሉ ወይም የሚተው ከሆነ ይቀጣሉ፡፡

### የሶላት ቅድመ ሁኔታዎች

1. ከትልቁም ሆነ ከትንሹ ሃደስ ንፁህ መሆን
2. አካል ፣ ልብስና የመስገጃው ቦታ ንፁህ መሆን
3. አውራን መሸፈን
4. ወደ ቂብላ መዞር
5. ሶላትን በወቅቱ መስገድ

**አውራ**: ማለት የተወሰኑ የሰውነት የአካል ክፍሎችን መሸፈን ሲሆን የወንድ ልጅ አውራው ከእንብርቱ እስከ ጉልበቱ ሲሆን የሴት ልጅ አውራ ደግሞ ከፊቷና ከመዳፏ በቀር ሙሉ አካሏ ነው፡፡

### የሶላት ወቅቶች

**የሱቢህ ወቅት**: ከንጋት ቀደም ብሎ ፀሐይ እስከ ምትወጣ ወይም ጎህ እስኪቀድ ድረስ ነው፡፡

**የዙሁር ወቅት**: የሚጀምረው ፀሐይ በአናት ትክክል ስትሆን ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ የአንድ እቃ ጥላው ከእቃው ጋር ተመሳሳይ መጠን ሲኖረው ነው፡፡

**የአሱር ወቅት**: የሚጀምረው የአንድ እቃ ጥላው ከእቃው በሁለት እጥፍ በሆነ ጊዜ ሲሆን ፀሐይዋ ስትገባ ያበቃል፡፡

**የመግሪብ ወቅት**: ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ስትጠልቅ የሚጀምር ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ ቀይ የሆነው አድማስ በስተምዕራብ በኩል በጠፋ ጊዜ ነው።

**የኢሻ ወቅት**: የሚጀምረው ቀዩ አድማስ ከምዕራብ በኩል ከጠፋ ጊዜ ጀምሮ ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ ከንጋት ቀደም ብሎ ነው።

## ጥያቄና መልስ

1) የሶላት ቅድመ ሁኔታዎች ምንምን ናቸው?
2) አውራ ማለት ምን ማለት ነው?
3) የአምስቱን የሶላት ወቅቶች ግለፅ?
4) የነፍል ሶላት መከሩህ(የተጠላ) የሚሆንባቸውን ጊዜያቶች አስረዳ?

# ክፍል 11

## አርካኑ ሶላት(የሶላት ምሶሶዎች)

በሶላት ውስጥ ግዴታ መደረግ ያለባቸው 13 ተግባራቶች አሉ። እነሱም አርካኑ ሶላት የሶላት ምሶሶዎች ተብለው ይጠራሉ።

1 ሶላት ለጀምር አሏሁ አክበር ከማለት በፊት ለመስገድ መነየት(ማሰብ)

2 የሚችል ሰው ቀጥብሎ መቆም

3 ከሶላቱ መጀመሪያ ላይ አሏሁ አክበር ማለት

4 ፋቲሃን መቅራት

5 ያለምንም መቻኮል በቀስታ ሩኩ  ማድረግ

6 ከሩኩዕ በኋላ ቀጥ ብሎ መቆም

7 ሁለት ሰጅዳ ማድረግ

8 በሁለት ሰጅዳ መካከል መቀመጥ

9 ከሶላቱ መጨረሻ ላይ መቀመጥ

10 በመጨረሻው መቀመጥ ላይ ተሸሁፍ ማንበብ

11 የመጨረሻው መቀመጥ ላይ ዱሩድ ማንበብ

12 እያንዳንዱን የሶላት ክፍል በተገቢው ቅደምተከተልና መረጋጋት ቀስብሎ መፈፀም

13 ሶላቱን በሰላምታ መጨረስ

### የኒያ ቅድሙ ሁኔታዎች

1. ሶላት ለመስገድ ስናስብ የትኛው ሶላት እንደሆነ መግለፅ ዙሁር ነው ወይስ አሱር
2. ለመስገድ የታሰበው ሶላት ቀዷነው ወይንስ ነዋፊል ነው የሚለውን መግለፅ

### የሱረቱል ፋቲሃ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ጠብቆ መቅራት
2. ከአንዱ በኋላ ሌላኛውን አያ ያለምንም ማዘግየት መቅራት
3. ተሽዲድ ያለውን እያንዳንዱን ፊደል በትክክል ማንበብ
4. ትርጉሙን የሚቀይር ስህተት አለመስራት
5. ሌሎች በሚሰሙት መልኩ ማንበብ
6. ከቁርአን ውጭ የሆነ ቃል አለመጨመር

### ሩኩዕ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ

1. ሁለቱንም እጆች ጉልበት ላይ በማድረግ ማጎንበስ
2. ጀርባንና እራስን በተመሳሳይ ደረጃ ቀጥ አድርጎ ማጎንበስ

### የሱጁድ ቅድመ ሁኔታዎች

1. በሰባቱ የአካል ክፍሎች በመታገዝ ሱጁድ ማድረግ
2. ግንባርን መሬት ላይ መድፋት ወይም ወለሉን ማስነካት
3. ሱጁድ ሲያደርጉ የሚንቀሳቀስ ወይም የሚዋልል ነገር ላይ አለማድረግ

## ጥያቄና መልስ

1. በሶላት ውስጥ ግዴታ የሆኑ ተግባራቶች ምን ያህል ናቸው?
2. የንያ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

## ክፍል 12

## ከሶላት በፊት ያሉ የሱና ተግባራቶች

የሚከተሉት ተግባራቶች ሶላት ከመጀመራችን በፊት ያሉ ሱናዎች ናቸው።

1. ለአምስቱ አውቃ ሶላት በተደነገገላቸው ጊዜ አዛን ማድረግ። ለፈጅር ሶላት ሁሉት ጊዜ አዛን ማድረጉ ሱና ነው። የመጀመሪያው አዛን የሚደርገው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሲሆን ሁለተኛው አዛን የሚደረገው ከንጋት በፊት ነው።
2. ፈርድ ሶላት ከመስገድ በፊት ኢቃማ ማድረግ
3. ሲዋክ መጠቀም
4. በፊትለፊት የሆነ ሰው እንዳያልፍ ወይም ቂብላ እንዳይሰብር ለማድረግ የሆነ እቃ ማስቀመጥ

**የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ**

1 የሶላቱ መጀመሪያ ላይ ወይም ሩኩዕ ስናደርግ ፣ ከርኩዕ ስንነሳና ከተሸሁድ ተነስተን አሏሁ አክበር ስንል ሁለቱንም እጆች እስከ ትከሻ ድረስ ከፍ በማድረግ መዳፋችነን ወደ ቂብላ ማዞር

2 የቀኝ እጅን በግራ እጅ ላይ በመደረብ ከደረት በታች ማስቀመጥ

3 የመከፈቻ ዱአ ማንበብ

4 ተአውዥ ማንበብ

5 ሱረቱል ፋቲሃን ከቀሩ ብኋላ ሌላ ሱራ ማንበብ። ኢማሙ ሲያነብ ተከታዮቹ ዝምብለው ያደምጣሉ

6 ድምፅን ከፍ አድርጎ በሚቀራባቸው የሶላት ወቅቶች ድምፅን ከፍ አድርጎ መቅራት

7 ከሩኩዕ ፣ ከሰጅዳ ሲነሱ እንዲሁም ሩኩዕ ሲያደርጉ አሏሁ አክበር ማለት

8 ሩኩዕና ሱጁድ ላይ ተስቢህ ማድረግ

9 ከሱረቱል ፋቲሃ ምንባብ ብኋላ አሚን ማለት

10 ከሩኩዕ ሲነሱ ሰሚአሏሁ ሊመን ሃሚዳ _ ረበና ወለከል ሃምድ ማለት

11 ከመጨረሻው መቀመጥ ውጭ በሁሉም ቁጭታዎች በግራ እግር ላይ መቀመጥ

12 የመጨረሻው መቀመጥ ላይ ግራ እግርን ወደ ፊት ትንሽ ወጣ በማድረግ መቀመጫን መሬት በማስነካት መቀመጥና የቀኝ እግር እንደዛው እንደሆነ ጣቶቹ ወደ መሬት እንደተተከሉ ወደ ቂብላ ማዞር

13 ሁለቱንም እጆች ታፋ ላይ ማድረግ

14 በሁለቱም ጎን ማሰላመት (አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱሏህ ማለት)

## በወንዶችና በሴቶች ሶላት መካከል ያለ ልዩነት

በወንዶችና በሴቶች ሶላት መካከል አራት ልዩነቶች አሉ። እነሱም፦

1. ወንድ ልጅ በሩኩዕ ወቅት ክንዱን ከደረቱ ማራቅ ያለበት ሲሆን ሴት ልጅ ግን ክንዷን ወደ አካሏ ጎን ማስጠጋት ይኖርባታል።
2. ወንድ ልጅ ሱጁድ ሲያደርግ ሆዱን ከታፋው ማራቅ ያለበት ሲሆን ሴት ልጅ ግን ሆዷ ታፋዋን ሊነካ በሚችል መልኩ ትታጠፋለች።
3. ወንድ ልጅ ድምፁን ከፍ አድርጎ መቅራት ያለበት ሲሆን ሴት ልጅ ግን በእያንዳንዱ ሶላት ለስለስ ባለ ድምፅ ነው መቅራት ያለባት በተለይ አጅነብይ ባለበት ቦታ ስትሰግድ።
4. ኢማሙ ስህተት ሲሰራ ወንዱ ተከታይ ሱብሃነሏህ በማለት የሚያስታውሰው ሲሆን ሴት ደግሞ በእጇ በማጨብጨብ ታስታውሳለች።

## ጥያቄና መልስ

1) ከሶላት በፊት ያሉ የሱና ተግባራቶች ምንድን ናቸው?
2) ሶላት ውስጥ ስንት የሱና ተግባሮች አሉ?
3) የሶላት አሰጋገድ ሁኔታን አብራራ?
4) በወንዶችና በሴቶች የሶላት አሰጋገድ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

# ክፍል 13

# ሶላት የሚያበላሹና የተጠላ የሚያደርጉ ተግባራት

### ሶላት የሚያበላሹ ነገሮች

1 በአይነ ምድር መውጫ በኩል ከሆድ አየር ማስወጣት

2 በአካል ወይም በልብስ ላይ ያረፈን ቆሻሻ ከማፅዳት ማዘግየት

3 አውራ ሲገለጥ አለመሸፈን

4 ሆንብሎ መናገር

5 መብላት መጠጣት

6 በስህተት ቢሆን እንኳ ሶስት ተከታታይ እርምጃ መራመድ

7 መዝለል

8 ከሶላቱ አካል ያልሆነን ነገር ሆንብሎ መጨመር

9 መሳቅ

10 ኒያን መቀየር

11 ሩኩዕን ወይም ሌላኛውን የሶላት ሸርጥ መተው

### ሶላት መክሩህ (የተጠላ) የሚያደርጉ ተግባራቶች

በሶላት ውስጥ ማከናወን የተጠሉ ብዙ ተግባራት አሉ። ነገርግን የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

1. ምንም ሳያስፈልግ ፊትን ወደ ጎን ማዞር
2. ወደ ሰማይ መመልከት
3. አንዱን እግር ከፊት ሌላኛውን ከኋላ ማድረግ ወይም አንድ ላይ ማገጣጠም
4. መትፋት ፣ መናፈጥ
5. ቀስ ተብሎ መቀራት ባለበት ወቅት ጮሆ መቅራትና ድምፅን ከፍ ተደርጎ መቀራት ባለበት ወቅት ድምፅን አጥፍቶ መቅራት

6. መቃብር ቦታ ላይ መስገድ

7. በአይነምድር ወይም በሽንት ተወጥሮ መስገድ

8. በጣም ተርቦ ወይም ምግብ ቀርቦ መስገድ

9. ጣቶችን ማንቀጫቀጭና ማጠላለፍ

## ጥያቄና መልስ

1) ሶላት የሚያበላሹ ነገሮችን ዘርዝሩ?

2) ሶላት ውስጥ ማከናውን የተጠሉ ነገሮች ምንምን ናቸው?

## ክፍል 14

## ነዋፊል

ሁለት አይነት ነዋፊሎች አሉ። እነሱም ረዋቲብና ገኢይሩ ረዋቲብ ናቸው።

**ረዋቲብ:** አምስቱን ፈርድ ሶላቶች ተከትለው የሚመጡ የነፍል ሶላቶች ማለት ሲሆን ሁለት አይነት የረዋቲብ አይነቶች አሉ። እነሱም ሙአከዳና ገኢይሩ ሙአከዳ ናቸው።

### ረዋቲብ ሙአከዳ

የረዋቲብ ሙአከዳ 10 ረከአቶች ናቸው። እነሱም፦

- 2 ረከአት ከፈጅር ሶላት በፊት
- 2 ረከአት ከዙሁር ሶላት በፊትና 2 ረከአት ደግሞ ከዙሁር በኋላ
- 2 ረከአት ከመግሪብ በኋላ
- 2 ረከአ ከኢሻ በኋላ

**ረዋቲብ ገኢይሩ ሙአከዳ** ስምንት ረከአቶች ናቸው። እነሱም፡-

- 2 ረከአት ከዙሁር ሶላት በፊት
- 4 ረከአት ከአሱር ሶላት በፊት
- 2 ረከአት ከኢሻ ሶላት በፊት

**ገኢይሩ ረዋቲብ** ማለት አምስቱን ፈርድ ሶላቶች አስከትለን ከምንሰግዳቸው ነዋፊል ሶላቶች ውጭ የሆኑ ሌላ ነዋፊል ሶላቶች ናቸው።

1. ዊትር: የሚሰገደው ከኢሻ በኋላ ነው።
2. ተራዊህ: ይህ ነፍል ሶላት የሚሰገደው በረመዷን ወር ከኢሻ ሶላት በኋላ ሲሆን 20 ረከአቶች አሉት።
3. ሶላቱ አዱሃ: አነስ ቢባል ሁለት ረከአ በዛ ቢባል ደግሞ ስምንት ረከአ ይሰገዳል። የዚህ ነፍል ሶላት ወቅት የሚጀምረው ፀሐይ ከወጣችበት በኋላ ሲሆን የሚያበቃው ደግሞ ፀሐይ  በአናት ትክክል እስክትሆን ድረስ ነው።
4. ተህያቱል መስጅድ: ወደ መስጅድ እንደ ገቡ ከመቀመጥ በፊት 2 ረከአት መስገድ ነው።
5. የሁለቱ ኢዶች ሶላት
6. የፀሐይና የጨረቃ ግርዶሽ ሶላት

## ጥያቄና መልስ

1) ስንት የነዋፊል ሶላት አይነቶች አሉ?
2) ረዋቲብ ምንድነው?
3) ገኢይሩ ረዋቲብ ምንድነው?

## ክፍል 15

## የጀመአ ሶላት

አምስቱን አውቃ ሶላቶች በጀመአ (በህብረት) መስገድ ፈርዱል ኪፋያ ሲሆን የጁምአ ሶላት እንዲሁ በጀመአ መስገዱ ፈርዱል አይን ነው።

### ኢማሙን የመከተል ቅድመ ሁኔታዎች

1. ኢማሙን ለመከተል መነየት(ማሰብ)
2. ኢማሙ ሳይነሳ አለመነሳት
3. የኢማሙን እንቅስቃሴ ማወቅ
4. ወደ ኢማሙ መቅረብ
5. ኢማሙን አለመቅደም አለመዘግየትም
6. ከኢማሙ በፊት ተክቢረቱ ተህሪም አለማድረግ
7. ኢማሙን በሱና መከተል

### በሶላት ወቅት ስግደት ላይ ልንከተለው የሚገባ ማነው

ማንኛውምንም አዕምሮው ጤናማ የሆነና ለአካለ መጠን የደረሰ ሙስሊምን ሁሉ በሶላት ላይ መከተል ይቻላል። ነገርግን ወንድ ልጅ ሴትን አይከተልም፤ ቁርአን ማንበብ የሚችል ቁርአን ማንበብ የማይችልን አይከተልም፤ ፈርድ ሶላት የሚይሰግድ ሰው ነፍል ሶላት የሚሰግድን ሰው መከተል አይፈቀድለትም።

## ጥያቄና መልስ

1) በጀመአ የመስገድ ውሳኔ ወይም ህግጋት ምንድነው?
2) ኢማሙን ለመከተል ቅድመ ሁኔታዎቹ ምንምን ናቸው?
3) በጀመአ ሶላት ልንከተለው የምንችለው ማንን ነው?

## ክፍል 16

## የተከታይ አይነቶች

ሁለት የተከታይ አይነቶች አሉ። እነሱም መስቡቅና ሙወፊቅ ናቸው።

**መስቡቅ**: ማለት ኢማሙ ሩኩዕ ከማድረጉ በፊት ፋቲሃን ለመቅራት ጊዜ ሳይኖረው ጀመአውን የተቀላቀለ ተከታይ ነው።

**ሙወፊቅ**: ኢማሙ ረኩዕ ከማድረጉ በፊት ፋቲሃን የመቅራት እድል ያገኘ ተከታይ ነው።

### መስቡቅን የተመለከቱ ውሳኔዎች(ህግጋቶች)

1. መስቡኡ ኢማሙን ሩኩዕ ላይ ሆኖ ካገኘው ፋቲሃን ሳያነብ ሩኩዕ ያደርጋል። ኢማሙን ቀስብሎ ሩኩዕ ላይ ካገኘው ረከአውን እንዳገኘ ይቆጠርለታል።
2. ኢማሙ እንደቆመ አግኝቶት ነገርግን መስቡኡ ፋቲሃን ሳይጨርስ ኢማሙ ሩኩዕ ቢያደርግ እሱም ተከትሎ ሩኩዕ ማድረግ ይኖርበታል።
3. ኢማሙ እንደቆመ አግኝቶት የመክፈቻ ዱአና ተአውዝ ማንበብ እንደ ጀመረ ኢማሙ ሩኩዕ ቢይልደርግ ለዱአውና ለተአውዙ የቆየበትን ያህል ጊዜ መቆየት አለበት። ከዚያ ብኋላ ኢማሙን ሩኩዕ እያደረገ ካገኘው ረከአውን እንዳገኘ ይቆጠርለታል። ነገርግን ማስቡኡ ሩኩዕ ከማድረጉ በፊት ኢማሙ ከሩኩዕ ቢነሳ(ቀጥ ቢል) ረከአውን እንዳጣው ይቆጠራል።

### ሙወፊቅን የተመለከቱ ውሳኔዎች

1. ሙወፊቁ ፋቲሃን መጨረስ ያለበት ሲሆን ሙወፊቁ ፋቲሃን ከመጨረሱ በፊት ኢማሙ ሩኩዕ ካደረገ እስከሚጨርሰው ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ያህል መቆየት ይኖርበታል።
2. ፋቲሃን ለመቅራት ትንሽ ሲቆይ ኢማሙን ከመከተል መዘግየቱ ይፈቀድለታል።

## ጥያቄና መልስ

1) ስንት የተከታይ አይነቶች አሉ?
2) መስቡዕ ማነው?
3) ሙወፌቅ ልንለው የምንችለው ማነው?
4) መስቡቅን የተመለከቱ ውሳኔዎች ምንድን ማቸው?
5) ሙወፌቅን የተመለከቱ ውሳኔዎችን ዘርዝር?

## ክፍል 17

## ሶላቱ ሙሳፊር(የምንገደኛ ሶላት)

አንድ መንገደኛ አራት ረከአ ካለው የፈርድ ሶላት ሁለቱን ብቻ ማሳጠሩ ይፈቀድለታል። እንዲሁም ዙሁርንና አሱርን አጣምሮ ዙሁር ላይ ወይም አሱር ወቅት፤ መግሪብና ኢሻን መግሪብ ላይ ወይም ኢሻ ወቅት ላይ አጣምሮ መስገድ ይቻላል።

### ሶላትን የማሳጠር ቅድመ ሁኔታዎች

1. አንድ ቀንና ሌሊት የሚሸፍን እርቀት ያለው ጉዞ መጎዝ
2. ለጊዜው የሆነ አንድ ቦታ ላይ ለማረፍ መነየት
3. ጉዞውን ሐራም የሆነ ነገር ለመፈፀም ተብሎ አለመሆን
4. ቀስር(ማሳጠር) የተፈቀደበት ሶላት ላይ ለእያንዳንዱ ሶላት ቀስር ለማድረግ ኒያ ማድረግ
5. የአካባቢው ነዋሪ የሆነ ኢማም አለመከተል

የመጀመሪያው የሶላት ወቅት ላይ ሁለት ሶላቶችን የማጣመር  ቅድመ ሁኔታዎች

1. የሶላት ወቅቱ መጀመር
2. የመጀመሪያውን ሶላት ሲሰግዱ አጣምሮ የመስገድ ኒያ ማድረግ
3. ያለምንም ማዘግየት እነሱን ማጣመር
4. የሁለተኛው ሶላት ወቅት ከመጀመሩ በፊት በጉዞ ላይ መሆን

ሁለተኛው የሶላት ወቅት ላይ ሁለቱን ሶላቶች የማጣመር ቅድመ ሁኔታዎች

1. የመጀመሪያውን ሶላት ሲሰግዱ የማዘግየት ኒያ ማድረግ
2. የሁለቱንም ሶላቶች ወቅት እስኪያበቃ ድረስ ጉዞውን መቀጠል

## ጥያቄና መልስ

1) ምንገደኛ ሰው እንዴት ነው ሶላት የሚሰግደው?
2) ሶላት የማሳጠር ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝር?
3) የመጀመሪያውና ሁለተኛው የሶላት ወቅት ላይ ሁለቶቹን ሶላቶች የማጣመር ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

# ክፍል 18

## የጁምአ ሶላት

የጁምአ ሶላት መስገድ በእያንዳንዱ አዕምሮው ጤናማ በሆነና ለአካለ መጠን በደረሰ ሙስሊም ላይ ሁሉ ግዴታ ነው።

**የጁምአ ሶላት ቅድመ ሁኔታዎች**

1. ከተማ ውስጥ መስገድ
2. ቢያንስ 40 ሰዎች በተገኙበት በጀመአ መስገድ
3. የዙሁር ወቅት ላይ መስገድ
4. ከሶላቱ በፊት ሁለት ሁጥባ ማድረግ
5. በዚኸው ከተማ ውስጥ ከጁመአ ሶላት በፊት ሌላ የጁምአ ሶላት ቀደም ብሎ አለመስገድ

**የሁለቱ ሁጥባ አርካኖች**

1. ኹጥባ የሚያደርገው ሰው ከትልቁና ከትንሹ ሐደስ(ቆሻሻ) የነፃ(የተጥራራ) መሆን አለበት።
2. ልብሱ ፣ አካሉ ፣ ቦታው ከቆሻሻ መፅዳት ይኖርበታል።
3. አውራው የተሸፈነ መሆን አለበት።
4. ኹጥባ የሚያደርገው ሰው የሚችል ከሆነ መቆም አለበት።
5. በሁለቱ ኹጥባ መካከል ምቹ በሆነ ሁኔታ ተደላድሎ መቀመጥ ይኖርበታል።
6. ታዳሚዎቹ ያዳምጡት ዘንድ ኹጥባው ከፍ ባለ ድምፅ መደረግ አለበት።
7. ከኹጥባው ቡኋላ ያለምንም ማዘግየት ወዲያውኑ ሶላቱ መጀመር አለበት።

**የጁመአ ሶላቱን ለመተው ወይም ሶላቱ የሚሰገድበት ቦታ ላለመሄድ የሚያስችሉ ነገሮች**

1. ህመም
2. አይነአማነት

3. ከባድ ዝናብ መጣል
4. አካለ ስንኩልነት

**ጁምአን እንዴት ማግኘት ይቻላል**

አንድ ረከአ ከኢማሙ ያገኘ ሰው ጁምአውን እንዳገኘ ይቆጠርለታል። ኢማሙ ካሰላመተ ብኋላ ቀሪውን ረከአ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመቅራት ይጨርሳል። ነገርግን ምንም አይነት ረከአ ከኢማሙ ካላገኘ ለጁምአ ሰላት ነይቶ ቀሪውን ሰላት የዙሁር ሰላት በመስገድ ይጨርሳል።

**በጁምአ ቀን ሱና የሆኑ ተግባራቶች**

1. ሻወር መውሰድ
2. ጥፍርን መቁረጥ
3. ሽቶ መነስነስ
4. ነጭ ልብሶችን መልበስ
5. ኹጥባውን ልብ ብሎ ማድመጥ
6. ወደ መስጅድ ሲሄዱ ተክቢራን ማለት

## ጥያቄና መልስ

1) የጁመአ ሰላቱን የተመለከቱ ውሳኔዎች ወይም ህግጋቶች ምንምን ናቸው?
2) የጁምአ ሰላት ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝሩ?
3) የሁለቱ ኹጥባ አስፈላጊ ክፍሎች ምንድን ናቸው?
4) የጁምአ ሰላት ላይ ላለመሄድ የሚይልስችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
5) የጁምአ ሰላትን እንዴት ማግኘት ይቻላል?
6) በጁምአ ቀን የሚፈፀሙ የሱና ተግባራትን ግለፁ?

## ክፍል 19

## የኢድ ሶላት

የሁለቱ ኢዶች ሶላት በአንድ አካባቢ ለሚኖርም ሆነ መንገደኛ ለሆነ ሰው ሱና ሙአከዳ ሲሆኑ ሁለት ረከአቶች አሏቸው። ወቅቱ ደግሞ ፀሐይ ከወጣችበት ጊዜ አንስቶ እስከ ምታጋድልበት ጊዜ ድረስ ነው።

### የኢድ ሶላት አሰጋገድ ሁኔታ

ከሶላቱ መጀመሪያ ላይ አሏሁ አክበር ማለት። ከዚያ ብኋላ የመክፈቻ ዱአና ተአውዝ ማንበብ። ከዚያም ተክቢራን ሰባት ጊዜ ማለት። ፋቲሃንና ሌላ ሱራን ድምፅን ከፍ አድርጎ መቅራት። በሌሎች ሶላቶች ላይ እንዳደረግነው ሩኩዕና ሱጁድ ማድረግ። ከሰጅዳ ለሁለተኛው ረከአ ሲነሱ ሌሎች ሶላቶች ላይ እንደሚደረገው ተክቢራ ማድረግና ከዚያ ብኋላ ተጨማሪ አምስት ተክቢራዎችን ማድረግና እንደተለመደው ሶላቱን መጨረስ። ሶላቱ ከተሰገደ ብኋላ ሁጥባ ያደርጋል። እንዲሁም በሁለተኛው ሰባት ጊዜ ተክቢራ አድርጎ ኹጥባ ያደርጋል።

### በኢድ ቀናቶች ሱና የሆኑ ተግባራት

1. ሻወር መውሰድ
2. ቆንጆ ቆንጆ ልብሶችን መልበስ
3. ድምፅን ከፍ አድርጎ ቤት ውስጥም ሆነ ገበያ ቦታ ተክቢራ ማለት እንዲሁም የኢድ ምሽት ንጋት ላይ አንስቶ ኢማሙ ሶላቱን እስኪጀምር ድረስ መንገድም ላይ ቢሆን ተክቢራ ማለት።
4. ከአረፋ ቀን ዙልሂጃ 9 ከፈጅር ጀምሮ እስከ አያም ተሽሪቅ ዙልሂጃ 13 ከእያንዳንዱ ሶላት ብኋላ ተክቢራ ማለት።

### ጥያቄና መልስ

1) ሁለቱን የኢድ ሶላቶች የተመለከተ ውሳኔ(ህግጋት) ምንድነው?
2) የኢድ ሶላት አሰጋገድ እንዴት ነው?
3) በኢድ ቀናቶች ሱና የሆኑ ነገሮችን ጥቀስ?

# ክፍል 20

# የጀናዛ ሶላት

### ለሞተ ሰው ግዴታ ሊፈፀሙ የሚገባ ተግባራቶች

1. አስክሬኑን ማጠብ
2. መከፈን
3. ለእሱ ሶላት መስገድ
4. መቅበር

### የአስተጣጠብ ሁኔታ

አስክሬኑን ሶስት ጊዜ ማጠብ፤ በመጀመሪያ በቁርቁራ ቅጠል ለሁለተኛ ጊዜ በውሃ ብቻና ለሶስተኛ ጊዜ በካምፉር ማጠብ። የሞተውን ሰው አካል በጨርቅ መሸፈኑ ፣ ከፍ ካለ ቦታ ማስቀመጥና የገላ ትጥበቱን ደበቅ ካለ ቦታ ማድረጉ ሱና ነው።

### የአከፋፈን ዘዴ

የወንድ አስከሬን በሶስት ጨርቅ የሴት አስከሬን ደግሞ በአምስት ጨርቆች  መከፈን ሱና ነው።

### የጀናዛ ሶላት ውስጥ ግዴታ የሆኑ ተግባራቶች

1. ኒያ ማድረግ
2. አራት ጊዜ ተክቢራ ማድረግ
3. ሱረቱል ፋቲሃን ማንበብ
4. ዱአ ማድረግ
5. ከሶስተኛው ተክቢራ ብኋላ ለሟቹ ዱአ ማድረግ
6. የሚችል ሰው ሶላቱን ቁሞ መስገድ
7. ማሰላመት

**የአቀባበር ዘዴ**

የአስክሬኑ ሽታ ወደ ውጭ ሊወጣ በማይችል መልኩና እንስሳት ሊያወጣው በማይችለው መልኩ መቅበር። አስክሬኑ ወደ ቂብላ በማዞር መቅበር ዋጅብ ነው።

**በሱና የመቅበር ዘዴ**

ቢያንስ የሟቹ ቁመትና ስፋት ጋር እኩል በሚሆን መቃብር ውስጥ በማስገባት ከፈኑን ከፊቱ በማስወገድ ወደ ቂብላ በማዞር ጉንጬን መሬት ላይ ማድረግ። ከዚያም ቀብሩን በጭቃ ወይም በአፈር መሸፈን። የቀብሩ ስነስርአት ሲያበቃ ለሟቹ ምህረትን መለመን ወይም ዱአ ማድረግ።

## ጥያቄና መልስ

1) ለሟች የሚደረግ ጉሱል (የገላ ትጥበት) እንዴት ነው?
2) አስክሬኑ የሚከፈነው እንዴት ነው?
3) በጀናዛ ሶላት ውስጥ ፈርድ የሆኑ ነገሮችን ዘርዝር?
4) የሱና አቀባበር ዘዴ እንዴት ነው?

## ክፍል 21

## ዘካ (የድሆች መዋጮ)

**ዘካ:** በአዕምሮው ጤናማ በሆነና ለአካለ መጠን በደረሰ ፣ ኒሷብ ባለው ማንኛውም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው።

### ዘካ ዋጅብ የሆነባቸው እቃዎች(ሃብቶች)

1. ላም ፣ ጎሽ ፣ ፍየል ፣ በግና ግመል ሲሆኑ ለአንድ የጨረቃ አመት ሙሉ ገላጣ የግጦሽ መሬት ላይ የጋጡና ከኒሷቡ በታች ያልሆኑ እንስሳት መሆን ይኖርባቸዋል።
2. ወርቅና ብር ሴቶች ለማጌጫነት ከሚጠቀሙበት ውጭ ያለ ወርቅ ፣ ብር እና ለአንድ የጨረቃ አመት ሙሉ ከኒሷቡ ጋር እኩል የሚሆን የንግድ ሸቀጦች
3. ከኒሷብ የሚደርስ ፍራፍሬና እህል

### የላምና የጎሽ ኒሷብ

የላም ወይም የጎሽ ኒሷብ ቢያንስ 30 ሲሆን በቁጥር ሰላሳ ከደረሰ ዘካ መስጠቱ ግዴታ ይሆናል። የአንድ አመት ላም ወይም ጎሽ ለሰላሳዎቹ በዘካነት የሚሰጥ ሲሆን የሁለት አመት ላም ወይም ጎሽ ደግሞ ለአርባዎቹ በዘካ መልክ ትሰጣለች። ለቀሪዎቹም ተመሳሳይ ቀመር ነው የምንጠቀመው።

### የግመል ወይም የፍየል ኒሷብ

የበግ ወይም የፍየል ኒሷብ 40 ሲሆን አርባ በጎች ወይም ፍየሎች ያሉት ሰው ዘካ በእሱ ላይ ግዴታ ይሆንበታል።

1. ሆኖም አርባ ፍየሎች ወይም በጎች ያሉት የአንድ ዓመት ወይም የሁለት ዓመት ፍየል ወይም በግ በዘካ መልክ ይሰጣል።
2. ሃያ አንድ ወይም መቶ ፍየሎች ወይም በጎች ያሉት ሁለት ፍየል ወይም በግ በዘካ መልክ ይሰጣል።
3. ሁለት መቶ በግና ፍየል ያሉት ሶስት በጎችን ወይም ፍየሎችን በዘካ መልክ መስጠት ግዴታ ይሆንበታል።

4. አራት መቶ ያለው አራት በጎችን ወይም ፍየሎችን ይሰጣል

5. ከአራት መቶ በላይ ያለው ለእያንዳንዱ መቶ አንድ በግ ወይም ፍየል ዘካ ያወጣል

**የግመል ኒሷብ**

1. የግመል ኒሷብ የሚጀምረው ከአምስት ሲሆን አምስት ግመል ያለው ዘካ መስጠት በእሱ ላይ ዋጅብ (ግዴታ) ይሆንበታል።

2. አምስት ግመሎች ያሉት አንድ በግ በዘካ መልክ ይሰጣል።

3. አስር ግመል ያለው ሁለት በግ ይሰጣል።

4. አስራ አምስት ግመል ያለው ሶስት በግ ይሰጣል።

5. ሃያ ግመል ያለው አራት በግ ይሰጣል።

6. ሃያ አምስት ግመል ያለው የአንድ አመት እድሜ ያለው ግመል በዘካ መልክ ይሰጣል።

7. ሰላሳ ስድስት ግመል ያለው የሁለት አመት እድሜ ያለው ግመል ይሰጣል።

8. አርባ ስድስት ግመሎች ያሉት የሶስት ዓመት እድሜ ያለው ግመል ይሰጣል።

9. ስልሳ አንድ ግመሎች ያሉት የአራት አራት ዓመት እድሜ ያላቸውን ግመሎች በዘካ መልክ ይሰጣል።

**የፍራፍሬና የእህል ኒሷብ**

የፍራፍሬና የእህል ኒሷብ የአጠቃላይ ምርቱ 1/20ኛው ነው። የእሩዝ ከሆነ 1/10ኛው ይሆናል።

**የወርቅና የብር ኒሷብ**

1. የወርቅ ኒሷብ 20 ሚስቃል ነው።

2. የብር ኒሷብ 200 ዲርሃም ሲሆን 1/2ኛው -2.5 የወርቅና የብር ዘካ መስጠት ግዴታ ነው።

**የሸቀጣ ሸቀጥ ኒሷብ**

የሸቀጣሸቀጡ ግምት በአመት ሲሰላ 7.5 ጡልሃ ወርቅ የሚደርስ ከሆነ ወይም 52.5 ጡልሃ ብር የሚሆን ከሆነ ከሸቀጣሸቀጡ ግምት 2.5 የሚሆነው በዘካ መልክ የሚሰጥ ይሆናል።

## ጥያቄና መልስ

1) ዘካን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን (ህግጋቶችን) አስረዳ?
2) ምንምን እቃዎች ወይም ንብረቶች ላይ ነው ዘካ ዋጅብ የሚሆነው?
3) የላም ወይም  የጎሽ ኒሷብ ምንድነው?
4) የበግ ወይም የፍየል ኒሷብ ምንድነው?
5) የፍራፍሬና የእህል ኒሷብን ግለፅ?
6) የወርቅና የብር ኒሷብን ግለፅ?
7) የሸቀጣሸቀጥ ኒሷብ ምን እንደሆነ አስረዳ?

## ክፍል 22

## ዘካቱል ፊጥር

እያንዳንዱ አዕምሮው ጤናማ የሆነና ለአካለ መጠን የደረሰ ሙስሊም የእሱና የቤተሰቦቹን ፍላጎት ከሚያሟላበት ሌላ ተጨማሪ ሃብት ንብረት ካለው ለእራሱና በእሱ ስር በሚተዳደሩ ቤተሰቦቹ ስም ዘካቱል ፊጥር መስጠቱ ግዴታ ይሆናል።

### ዘካቱል ፊጥር የሚሰጠው ምን ያህል ነው

አራት እፍኝ የሚሆን ምግብ ፣ 4kg በቆሎ ወይም ከዚህ ጋር ተመጣጣኝ የሚሆን ጥሬ ገንዘብ በዘካቱል ፊጥር መልክ ይሰጣል።

### ዘካቱል ፊጥር የሚሰጠው መቼ ነው

ዘካቱል ፊጥር የሚሰጠው የመጨረሻው የረመዷን ቀን ፀሃይ ከመጥለቋ በፊት ሲሆን ረመዷን ሲጀምር መስታጠቱም ይፈቀዳል። ነገርግን ወደ ኢድ ሶላት ከመሄድ በፊት መስጠቱ በላጭ ነው። ከኢንድ ሶላት በኋላ መስጠቱ ግን የተከለከለ ነው።

### ዘካቱል ፊጥር ሊሰጠው የሚገባ ማነው

ፊጥሩ ሊሰጣቸው የሚገባ የሚከተሉት ስምንት አይነት ሰዎች ሲሆኑ ዘካቱል ፊጥር በሚከፍሉ ሰዎች ከተማ ውስጥ የሚኖሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

1. **ፍቀራ**: መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ከሚያሟሉበት በላይ ያላቸው ነገርግን ከኒሷቡ ጋር እኩል የሚሆን ሃብት ንብረት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።
2. **ሚስኪኖች:** ለዕለት ተዕለት ምግባቸው የሚሆን ነገር አጥተው ለመለመን የተገደዱ ችግረኞች ናቸው።
3. **ሙአለፈቱል ቁሉብ:** ልቦቻቸው በኢማን ገመድ የተሳሰረ ሰዎች፤ ሃብታሞችም ቢሆኑም እንኳ እነሱም ያጠቃልላል።
4. **ወል አማሊን:** የዘካውን ገንዘብ እንዲያስተዳድሩ የተሾሙ ሰዎች።
5. **ሪቃብ**

6. **አል ጋአሪሚን:** በራሳቸው መክፈል የማይችሉትን ከባድ እዳ የትጫናቸው ሰዎች

7. **ፊ ሰቢሊላህ (ሙጃሂድ):** እራሳቸውንም ሆነ ማህበረሰባቸውን ከወራሪ ሃይል ለመከላከልና የአሏህን ቃል የበላይ ለማድረግ የሚታገሉ ሰዎች ናቸው።

8. **ኢብኑ ሰቢል:** ቤታቸው ሃብታሞች ቢሆኑም እንኳ በጉዟቸው ላይ አስፈላጊውን ነገር ያልያዙ በአሏህ መንገድ የሚጓዙ መንገደኞች ናቸው።

### ዘካ የማይሰጣቸው ሰዎች

1. ሃብታሞች
2. ባሪያ
3. ካፊሮች (ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች)
4. መጠቃቀሚያቸው ዘካ በሚሰጠው ሰው ላይ የተመሰረተ የሆኑ ሰዎች
5. ከበኑ ሃሽም ቤተሰቦች መካከል የሆነ ሰው
6. ከበኑ ሙጠሊብ ቤተሰቦች የሆነ
7. ዘካ ሃራም ለሆነ ነገር የሚጠቀም ሰው

## ጥያቄና መልስ

1) ዘካቱል ፊጥርን የሚከፍለው ሰው ማነው?
2) ዘካቱል ፊጥር መከፈል ያለበት ምንያህል ነው?
3) የዘካቱል ፊጥር ተቀባዮች እነማን ናቸው?
4) ዘካቱል ፊጥርን የማይቀበሉት እነማን ናቸው?

## ክፍል 23

### ፆም

በረመዷን ወር ለመፆም በመነየት ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች ሁሉ ተቆጥቦ ቀኑንም ሌሊቱን በኢባዳ ማሳለፍ ነው።

**መፆም ያለበት ማነው**

***ፆም***: አዕምሮው ጤናማ በሆኑና ለአካለ መጠን በደረሱ ሙስሊሞች ላይ ሁሉ ግዴታ ሲሆን ሃይድና ኒፋሷ ላይ የሆኑ ሴቶች ግን መፆም አይፈቀድላቸውም።

**ፆም የሚጀምረው መቼ ነው**

የሻዕባን ወር ሰላሳ ቀን በሞላው ጊዜ ወይም የረመዷን ወር አዲሷ ጨረቃ በታየች በቀጣዩ ቀን ፆሙ ይጀመራል።

**ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች**

1. አውቆ ወይም ሆንብሎ ማስታወክ
2. የሆነ ነገር በአፍ ወይም በአፍንጫ በኩል ወደ ጉሮሮ መውረድ
3. ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ
4. አውቆ በራስ መርጨት
5. ሐይድ(የወር አበባ)
6. ከወሊድ ቡኋላ የሚፈስ ደም
7. መክፈር(ክህደት)

**አለመፆም የተፈቀደላቸው ሰዎች**

1. መፆም የበለጠ ጉዳት እንዳያደርስበት የሚፈራ በሽተኛ
2. ረዥም ጉዞ የሚጓዝ ሰው
3. ነፍሰጡር ወይም የምታጠባ ሴት መፆሟ እሷ ላይ ወይም ልጇ ላይ ጉዳት ያስከትልብናል ብላ የሰጋች ሴት
4. በጣም የሸመገለ ሰው

**ያለፈው ፆም ቀዷ**

አለመፆም የተፈቀደለት ሰው ያለፈውን ፆም ቡኋላ ላይ ቀዷውን ብቻ ማውጣት ይኖርበታል። ነገርግን ነፍሰጠር ወይም የምታጠባ ሴት ቀዷውን ማውጣትና ከዘካቱል ፊጥር ጋር እኩል የሚሆን ፊዳያ ለእያንዳንዱ ፆም መስጠት ይኖርበታል። በጣም አርጅቶ ለመፆም የማይችል ወይም በጣም ታሞ በከፊል በማገገም ላይ ያለ ሰው ላለፈው ለእያንዳንዱ ፆም መስጠት አለበት።

**የፆም ሱናዎች**

1. ሱሁርን ማዘግየትና ኢፍጣር ላይ ቶሎ ማፍጠር
2. በተምር ወይም በውሃ ማፍጠር
3. ከዘለፋና ከመጥፎ ንግግሮች መቆጠብ
4. በተቻለ መንገድ ሶደቃ መስጠትና ቁርአን መቅራት

**ፆምን በግብረ ስጋ ግኑኝነት ማበላሸት**

ፆሙን ግብረስጋ ግኑኝነት በማድረግ ያበላሸ ወይም ያፈረሰ የፆሙን ቀዷና ከፋራውን ማውጣት አለበት።

**ከፋራ**: ሙስሊም ባሪያን ነፃ ማድረግ ሲሆን ይህ ማድረግ ካልተቻለ ለተከታታይ ሁለት ወራት መፆም ይኖርበታል። ይህም ካልተቻለ ስልሳ ድሆችን መመገብ ወይም ለእያንዳንዳቸው 2kg ምግብ መስጠት።

**መፆም የተከለከለባቸው ጊዜያት**

1. የኢዱል ፊጥር ቀን
2. የኢዱል አዱሃና የተሽሪቅ ቀናቶች
3. በጥርጣሬ ቀን ፣ የሽዕባን ሁለተኛው አጋማሽ

**መፆም የሚወደድባቸው ቀናቶች**

1. ሰኞ ቀን
2. ሐሙስ ቀን
3. በጨረቃ ወር እያንዳንዷን 13ኛ ፣ 14ኛ ፣ 15ኛ ቀናት
4. ከኢዱል ፊጥር ብኋላ ያሉት ስድስት ቀናት
5. የአረፋ ቀን 9ኛው ዙልሂጃ
6. የአሹራ ቀን 10ኛው ሙሃራም(ከቀኑ ቀድሞ ወይም ቀኑን ተከትሎ)

**ለሞተ ሰው የሚደረግ ፆም**

ያለፈውን ፆም ቀዷ ሳያወጣ ለሞተ ሰው ወራሾቹ ወይም የቅርብ ዘመዶቹ 60 ድሆችን መመገብ ወይም በእሱ ፈንታ መፆም ይኖርባቸዋል። ከሟቹ ፍቃድ ያገኘ ወይም ወራሾቹ በእሱ ፈንታ እብዲፆሙ ይፈቀድላቸዋል።

## ጥያቄና መልስ

1) የፆም ፍች ምንድነው?
2) ፆም ግዴታ የሆነው በማን ላይ ነው?
3) ፆም የሚያበላሹ ነገሮችን ዘርዝሩ?
4) አለመፆም የተፈቀደላቸው እነማን ናቸው?
5) የፆም ሱናዎችን ጥቀስ?
6) ከፋራ ምንድነው?
7) መፆም የተከለከለባቸው ቀናት የትኞቹ ናቸው?
8) መፆም የሚወደድባቸው ቀናቶች የትኞቹ ናቸው?

## ክፍል 24

## ሐጅና ኡምራ

ሐጅና ኡምራ ማድረግ በሚችል አዕምሮው ጤናማ በሆነና ለአካላ መጠን በደረሱ ሙስሊሞች ላይ ሁሉ በህይወት ዘመን አንዴ ማድረጉ ፈርድ (ግዴታ) ነው።

### በሐጅ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች

1. ኒያ ማድረግ
2. አረፋ ላይ መቆየት
3. ጠዋፍ ማድረግ
4. ሰኢይ ማድረግ
5. የራስ ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር

**የሐጅ ግዴታዎች**

1. ከሚቃ ኢህራም መልበስ
2. ሙዝደሊፋ ውስጥ ለአንድ ምሽት ማሳለፍ(መቆየት)
3. አንድ ምሽት ሚና ውስጥ ማሳለፍ
4. የጀመራት ረሚ ማድረግ
5. መካን ትተው ሲሄዱ ጠዋፍ ዊዷ ማድርግ

**የሐጅ ሱናዎች**

በሐጅ ውስጥ ብዙ የሱና ተግባራቶች አሉ። የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

1. ኢህራም ከመልበስ በፊት ሻወር መውሰድ
2. አረፋ ላይ ከመቆየት በፊት ሻወር መውሰድ(መታጠብ)
3. በተሽሪቅ ቀናቶች የጀመራት ረሚ ከማድረግ በፊት መታጠብ
4. ኢህራሙን ከመልበስ በፊት ሽቶ መነስነስ
5. ልክ እንደ አንሶላ ወይም ፎጣ ያለ አዲስ ነጭ ልብስ መልበስ
6. ተልቢያ ማንበብ
7. ዚክር ማድረግ አሏህን ማስታወስ
8. መሻሪል ሐረም ላይ መቆየትና ዱአ ማድረግ

**በኢህራም ሁኔታ ላይ የተከለከሉ ተግባራቶች**

1. የተሰፉ ልብሶችን መልበስ(ለወንዶች)
2. እራስን መሸፈን(ለወንዶች)፤ ለሴቶች ደግሞ ፊትንና መዳፍን መሸፈን
3. ሽቶ መነስነስ
4. ፀጉርን ቅባት መቀባትና ማሳጠር

5. ጥፍርን መቁረጥ
6. ግብረ ስጋ ግኑኙነት ማድረግ
7. ማግባት
8. እንስሳትን ማደን
9. የሃረምን ዛፍ መቁረጥ

## ጥያቄና መልስ

1) ሐጅን የተመለከቱ ህግጋቶች ምንምን ናቸው?
2) የሐጅ ግዴታዎች ምንምን ናቸው?
3) በሐጅ ውስጥ ምን ያህል የሱና ተግባራት አሉ?
4) በኢህራም ሁኔታ ውስጥ የተከለከሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?
5) በኢህራም ሁኔታ ላይ የተከለከለ ተግባራትን የመፈፀም ውሳኔ(ህግጋት) ምንድነው?

## ክፍል 25

## የጠዋፍና የሳኢ ቅድመ ሁኔታዎች

### የጠዋፍ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ትልቁንና ትንሹን ሐደስ(ቆሻሻ) ማስወገድ
2. ሰትራን መሸፈን
3. የግራ ትካሻን ወደ ሐጀረል አስወድ በማዞር መጀመር
4. ካዕባን በግራ ትከሻ በኩል በማድረግ ጠዋፍ ማድርግ
5. ከጠዋፍ ውጭ ሌላ ነገር አለማድረግ
6. ሰባት ጊዜ ጠዋፍ ማድረግ
7. ጠዋፍ ለማድረግ መነየት

### የሳኢ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ከጠዋፍ በኋላ ሰኢ ማድረግ
2. ሰኢውን በሶፋ በመጀመር በመርዋ መጨረስ
3. ሰኢውን ሰባት ጊዜ ማድረግ

### ሐጅን የሚያበላሹ ነገሮች

ግብረስጋ ግኑኝነት ሆን ብሎ በተፈፀመ ጊዜ ሐጅን ያበላሻል። ነገርግን የሐጁ ስነስርአትና ቀደ፯ው መፈፀም አለበት። ድንበር ያለፈው መቀጫውን ግመል መስዋዕት ማድረግ ይኖርበታል። ካላገኘ ላም ማረድ ይኖርበታል። ካልቻለ ሰባት በጎችን ማረድ ይኖርበታል። አሁንም ካልሆነ ከግመሉ ዋጋ ጋር እኩል የሚሆን ምግብ ገዝቶ ለድሆች ማከፋፈል ይኖርበታል።

### ሐጅ ማድረግ ያልቻለ

እድሜው ገፍቶ ወይም ታሞ የማገገም ተስፋ የሌለው ሰው የሆነ ሰው ለእሱ ሐጅ እንዲያደርግለት መላክ ይኖርበታል።

## ጥያቄና መልስ

1) የጠዋፍ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

2) ሐጅ የሚያበላሹ ተግባራትን ዘርዝር?

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደውሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!